የአማራ ክልል

ባለፉት15 ዓመታት (1985-2001) በክልሉ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች (መስከረም 2002 ዓ.ም)

1.የግብርናና ገጠርልማት ስራዎች ዋና ዋና አፈጻጸሞች

ባለፉት ሁለት የመርሃ ግብር አመታት (ከ1987-1992 እና ከ1993-2001)የነበረው ሁኔታ

- ከፍተኛ የግብርና ምርት ጭማሪ በተከታታይ ተመዝግቧል::
- በምግብ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል የነበረው ሰፊ ክፍተት እየጠበበ መጥቷል::

1.1. የሰብል ምርት

አመታዊ የሰብል ምርት በያመቱ እየጨመረ ነው::
ምርት ለስድስተኛ ጊዜ በተከታታይ ዕድገት አሳይቷል::
የሰብል ምርት እድገት በተከታታይ በ15%፣
ምርታማነቱም ከ14 ኩንታል በሄክታር ወደ 17 ኩንታል በሄክታር ከፍ ብሏል::
የመቶ ሺዎች አ/አደሮች ኑሮም በከፍተኛ ደረጃ ተለውጧል::

የሰብል ምርት አመታዊ እድገት

ተቁ	ዝርዝር ሥራ	1986/87	2000/001
1	የለማ መሬት ስፋት በሄክታር		
	መኸር	2,608,320	4,05,1963
	በልግ	172,000	166,000
	መስኖ	44,366	347,725
2	የተገኘ ምርት መጠን በኩንታል		
	መኸር	23,846,130	60,614,094
	በልግ	507,300	1,058,103
	መስኖ	1,572,632	38,001,507

በ2001 ከ63 ሺህ ሄክታር በላይ ኮትቻ አፈር አጠንፍፎ ማልማት ተችሏል::
በዚህም ምክንያት ላለፉት በርካታ ዓመታት ከምርት ውጭ ሆነው የቆዩና ቢያመርቱም ምርታማነታቸው በእጅጉ አሽቆልቁሎ የቆዩ መሬቶች ላይ ምርትን ከ 3 እና ከዚያ በላይ እጥፍ ማሳደግ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሮአል::
አሲዳማ አፈርን ማልማት በ1,224 ሄ/ር መሬት ላይ ተከናውኗል::

የመስኖ ልማት

- በመስኖ ሊለማ የሚችለውን መሬት 1986/87 ከ 60 ሺ. ወደ 347ሺ. ሄ/ር (በ57%) ማሳደግ ተችሏል::
- በምርት ከ1.6 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 38 ሚሊዮን ኩንታል፤
- በምርታማነት ከ43 ኩንታል በሄክታር ወደ 60 ኩንታል በአማካይ ከፍ ሊል ችሏል::

የሽንኩርት ልማት በመስኖ (ፎገራ)

ውሃ ማቆር (ጅኦ ሜምብሬን)

የሽንኩርት ምርት (ፎገራ)

የአፕል ፍራፍሬ ልማት

የፒር ፍራፍሬ ልማት

1.2. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት

በግብርና ልማት ሥራ ረገድ ስነ ምህዳርን መሰረት በማድረግና ክልሉን ዕርጥበት አጠርና በቂ ዕርጥበት ባላቸው አካባቢዎች በመክፈል ከየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚተገበሩ ፓኬጆች ተቀርፀው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአርሶ አደሩ ተሞክረው ወጤታማ የሆኑትን በፓኬጅ በመቀመር ሁሉም አርሶ አደር እንዲፈፅማቸው ለማድረግ ወይም የማስፋት ስትራቴጅ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ይህንንም ለማገዝ ሙያተኛን በሚፈለገው ደረጃና መጠን ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣ ይህንኑ ለማሟላት ስፊ የአመለካከት፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች ተካሂደዋል፡፡

የኢክስቴንሽን አገልግሎት ሽፋንን በተመለከተ የገጠር ቀበሌዎች በኤክስቴንሽን አገልግሎት 100 % ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የተጠቃሚ አርሶ አደር ቁጥርን በተመለከተ ከ 2.3 ሚሊዮን በላይ አርሶ አደር የኤክስቴንሽን ድጋፍ በማግኘት ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በክልሉ ከ10 ሺህ በላይ የቀበሌ ሙያተኞች አሉን፡፡

2,784 የገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማት በየቀበሌው የተገነቡ ሲሆን፣ ከነዚህ ወስጥ 2,119 ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ (88% ያህሉ ቀበሌዎች ተሸፍነዋል)

በገጠር ብድር አቅርቦት ረገድ በየዓመቱ እስከ ብር 828.3 ሚሊዮን ብር የሚደርስ የተለያየ ብድር ለአርሶ አደሩ ተሰጥቷል፡፡

1.3 የማዳበሪያና የምርጥ ዘር አቅርቦት

ባለፉት የልማት ዓመታት የነበረው የማዳበሪያና የምርጥ ዘር አቅርቦት በከፍተኛ ደረጃ አድጓል።

በዚህም መሰረት በ1988 ዓ/ም 424 ሺ.ህ ኩንታል የነበረው የማዳበሪያ አቅርቦት በ2001 ወደ 1.65 ሚ/ኩንታል ሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያ ማቅረብና ጥቅም ላይ ማዋል የተቻለ ሲሆን፤ ከ28ሚሊዮን/ሜ/ኩብ በላይ ኮምፖስት ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ውሎአል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በምርት ዘመን ይቀርብ የነበረው ምርጥ ዘር ከ20.6 ሺ.ህ ወደ 74.5 ሺ.ህ ኩንታል ከፍ ብሏል።

በአርሶ አደር ማሳ የምርጥ ዘር ማባዛት ሥራ

1.4 ሁለገብ የህብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ

የማህበራት ሚና

- ሁለገብ የህብረት ስራ ማህበራት ለምርትና ምርታማነት እድገት መሪ ተዋንያን ናቸው፡፡
- ብዛታቸው 5,662 የሆኑ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተዋል፡፡
- የመሰረታዊ ማህበር አባላት ብዛት ወንድ 1,877,275 ሴት 407,524 በድምሩ 2,284,799 ሲሆኑ ካፒታላቸው ብር 318,610,079 ነው፡፡
- 43 ዩኒየኖች ተቋቁመዋል፡፡
- 1,223 መሰረታዊ ማህበራትን በአባልነት አቅፈዋል፡፡
- 108,268,257 ካፒታል አላቸው፡፡
- የካፒታል አቅም 135 ሚሊዮን ብር ደርሷል፡፡
- ለ5,957 የሰው ሀይል የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል፡፡
- በአሁኑ ጊዜ 100% የገጠር ቀበሌዎች በሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የታቀፉ ሲሆን፤ ከክልሉ አርሶ አደር 71 % በኅብረት ሥራ ማኅበር አባልነት ታቅፏል፡፡

1.5 የእንስሳት ሃብት ልማት

የእንስሳትን ዝርያ ለማሻሻል የውጭ ዝርያ ያላቸውን እንስሳት ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በእንስሳት ጤና ጥበቃ ረገድ በ1992 ዓ.ም 39 በመቶ ብቻ የነበረው የጤና አገልግሎት ሽፋን አሁን ወደ 80 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

የእንስሳት ጤና ተቋማትን በተመለከተም ለሦስት ቀበሌ አንድ ክሊኒክ ተቋቁሞ በ1992 ዓ.ም 20 በመቶ ብቻ የነበረው ሽፋን ወደ 84% ደርሷል፡፡

በእንስሳት ተዋጽኦ በኩልም ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ለማዕከላዊ ገበያ እንዲቀርብ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በደሴ ዙሪያ ወረዳ የወ/ሮ አበቡሽ የወተት ከብት እርባታ

በደጋ ዳሞት ወረዳ የዋሸራ በግ ዝርያ

የተመረተ የዓሣ ምርት በኩንታል



1.6 የምግብ ዋስትናና ሰፈራ ፕሮግራም

በሠፈራ ኘሮግራም ረገድ ከ1995 -2001 ዓ.ም ድረስ 82,196 የቤተሰብ ኃላፊዎች /166,194 ሕዝብ/ ለም በሆኑ አካባቢዎች እንዲሠፍሩ ተደርጓል፡፡

39,407 የቤተሰብ ኃላፊዎች /95,121 ሕዝብ/ ወይም 57.2% ተረጋግተው ኑሯቸውን በመምራት ላይ ይገኛሉ፡፡

1.7 የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎች

አፈርና ውሀ ጥበቃ

በአጠቃላይ ከ1987-1999 በድምሩ 3.4 ሚሊየን ሄ/ር መሬት ላይ የአፈር ጥበቃ ሥራ ተሠርቷል፡፡በተካሄደው ቆጠራ መሰረት ሳይፈርስ የተገኘው 1,808,866 ሄ/ር ወይም ከተሰራው 53% ነው፡፡ የተፋሰስ ልማት አስተሳሰብ /approach/ በቅርብ እየጐላ የመጣ ቢሆንም፤ በ1995 ዓ.ም ከ260 ተፋሰሶች ያልበለጠው አፈጻጸም እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ

ተፋሰስ መለየት - 30,041

ተፋሰስ ማጥናት - 8,622 ሊሆን ችሏል፡፡

የአፈር ጥበቃ እርከን ሥራ

ደን ልማትና ጥበቃ

የችግኝ ማፍላት ሥራ በ1989 ዓ.ም 318 ሚሊየን ብቻ የነበረ ሲሆን፤ በ2000 ዓ.ም ወደ 1.2 ቢሊየን ደርሷል።

በተመሣሣይ ደረጃ የችግኝ ተከላ ሥራም በ1989 ከነበረበት 37,400 ሄ/ር በ2001 ዓ.ም ወደ 89,800 ሄ/ር እድገት አሳይቷል።

በአጠቃላይ 448,000 ሄ/ር መሬት በሰው ሠራሽ ተከላ ተሸፍኗል።

በ2001 የችግኝ ተከላ አፈፃፀም ካለፉት አመታት በተሻለ 907 ሚሊዮን ደርሷል።

ያለፈው ዓመት የመፅደቅ ሁኔታ ሲታይ በሁለተኛ ዙር ግምገማ 65% ሆኖ ተገኝቷል።

የክልሉ የግብርናና ገጠር ልማት የእርሻ መሣሪያዎች ስርጭት (ከ1996-2001 ዓ/ም)

	1996	1997	1998	1999	2000	2001
ቢቢኤም	1350	2048	0	35	1689	17520
ታይሬጀር	8749	6391	5292	254	5220	12721
ትሪድል ፓምፕ	1	690	1883	71	899	-
ጠንካራ ክንድ	9480	3556	8196	90	6795	-
ጅኦ ሜምብሬን	-	-	-	-	-	36175

የክልሉ የምርጥ ዘር አቅርቦትና ስርጭት (ከ1996-2001 ዓ/ም)

	1996	1997	1998	1999	2000	2001
አቅርቦት	34256	66684.85	56842.31	50094.85	68790.33	74521
ስርጭት	30256	56373.9	43985.54	46753.6	58703.27	55000

በክልሉ የተለያዩ ኩሬዎችና ገንዳዎች የተጨመሩ የዓሣ ጫጩት ብዛት

1995	1996	1997	1998	1999	2000	2001
43900	6117	13270	22600	27071	-	-

የክልሉ የማዳበሪያ ስርጭት

	1996	1997	1998	1999	2000	2001
ዳፕ	421922	528452	679967	747668	798408	-
ዩሪያ	270561	356183	399634	476065	510590	-
					ድምር	1.4ሚሊየን

ትምህርት

በ1985 ዓ.ም የአማራ ክልል የከተማና የገጠር የትምህርት ሽፋን 13.6% የነበረ ሲሆን፣ በወቅቱ የነበሩት ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት ደግሞ 400 ሺህ፣ አገልግሎት የሚሰጡት የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ቁጥርም 2,386 ብቻ ነበር። ሆኖም ግን ከ1985 ዓ.ም ወዲህ ባሉት ጊዜያት አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። በአሁኑ ወቅት ከ10 ሺህ በማያንሱ የትምህርት ተቋማት አማካኝነት 4.1 ሚሊዮን ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተጠቃሚ ሆነዋል። ክልሉ በ1985 ዓ.ም የነበሩት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 83 ብቻ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት 213 የ2ኛ ደረጃ (የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ) እና 117 (11ኛ እና 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ) የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ት/ቤቶች፣ 53 የቴክኒክና የሙያ ተቋማትና 14 የሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች አሉት።

በ1984ዓ.ም በጎንደር፣በደሴና በደብረብርሃን ብቻ የነበሩት 3 የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ዛሬ ደረጃቸው ወደ ኮሌጅነት ቁጥራቸውም ወደ 10 አድጓል። በክልሉ ውስጥ አምስት ዩኒቨርሲቲዎች በመንግስት ተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ሁለት ተጨማሪ ዩኒቨርሲቲዎችም በመገንባት ላይ ናቸው። በሌላ በኩል ለግሉ ዘርፍ በተፈጠረው ምቹ ፖሊሲ 49 የግል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ተቋቁመው የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ። ከእነዚህ ውሱን መረጃዎች ብቻ በመነሳት ክልሉ በአበረታች የትምህርት ልማት እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ መገንዘብ ይቻላል።



ጤና

ከዛሬ 17 ዓመት በፊት በክልሉ የሚገኙ የጤና ተቋማት ቁጥር እጅግ ጥቂት ነበር። በዚህም ላይ የሙያተኞችና የመድሃኒት አቅርቦት እጥረቶች ተደምረው ችግሩን አባብሰውት ቆይተዋል። በዚሁ ምክንያት በቀላሉ በሚድን በሽታ ተይዘው ሕክምና ፍለጋ ላይ ታች ሲሉ የባዘኑትና ለህልፈተ ሕይወት የተዳረጉት በጣም ብዙ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት የአማራ ክልል ብሔራዊ በጤናው ዘርፍ አበረታች ደረጃ ላይ ይገኛል። በክልሉ በ1985 ዓ.ም 450 ክሊኒኮች፣ 39 ጤና ጣቢያዎችና 6 ሆስፒታሎች ብቻ የነበሩ ሲሆን፣ በ2001 ዓ.ም ክልሉ 2,828 ጤና ኬላዎች፣ 254 ጤና ጣቢያዎችና 17 ሆስፒታሎች አሉት። በተጨማሪም 300 ጤና ጣቢያዎችና 7 ሆስፒታሎች እየተገነቡ ናቸው።

ከሁሉም በላይ በሁሉም በክልሉ የገጠር ቀበሌዎች ሁለት ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ስልጥነውና ተመድበው የአብዛኛዎቹ የጤና ችግሮች መንስኤ የሆኑትን ችግሮች በቀላሉ መከላከልና በህብረተሰቡ ንቅናቄ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛሉ። በተለይም የእናቶችና ህፃናትን ስቃይና ሞት በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ያላቸውን ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሏል።

ኢንቨስትመንት

በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ይገኛል፡፡ እስከ መስከረም 30/2001 ዓም ባለው ጊዜ ውስጥ 65.7 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ 5053 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተዋል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ከ1.2 ሚሊዮን በላይ የስራ ዕድል ይፈጥራሉ፡፡ እስከ መስከረም 2002 ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ሥራ የጀመሩ የካፒታል መጠናቸው 2.98 ቢሊዮን የሆኑ 896 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ለ195,160 ወገኖች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካገኙት መካከል ሥራ የጀመሩ ፕሮጀክቶች

ዘርፍ	የፕሮጀክት ብዛት	ካፒታል በሚሊዮን	የተፈጠረ የሥራ ዕድል
ግብርና	455	246.5	174,165
ኮንስትራክሽን	82	213.95	2,704
ኢነርጂ	3	5,09.86	34
ሆቴል እና ቱሪዝም	123	364.6	4,782
ኢንዱስትሪ	109	1,220.1	6,671
ማህበራዊ	107	376.18	6,039
ንግድ	17	51.42	765
ጠቅላላ ድምር	896	2,982.61	195,160

መሠረተ ልማት

የመሠረታዊ ልማት አውታሮች ግንባታ ለአገራችን ኢኮኖሚ ፈጣን እድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በመሆኑም ክልሉ እንደ ክልል ከተቋቋመበት ከ1985 ዓም ጀምሮ በመንገድ፣ በኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት እና በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ እጅግ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል።

መንገድ

ክልሉ ሲቋቋም ከነበሩት 138 ወረዳዎች

መካከል 38 ያህሉ ከዞን ማዕከሎቻቸው ጋር የሚያገናኝ ምንም አይነት መንገድ አልነበራቸውም።

የአንዳንድ ወረዳ ነዋሪዎች ወደ ዞን ከተሞች ደርሶ ለመመለስ በእግር እስከ ሦስት ቀን ለመጓዝ ይገደዱ ነበር።

በአሁኑ ወቅት በክልሉ ውስጥ 6,669.1 ኪ.ሜ. ርዝመት ያላቸው መንገዶች የሚገኙ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 3,952 ኪ.ሜ. በፌዴራል መንግስት፣ 2,716.8 ኪ.ሜ. ደግሞ በክልሉ የገጠር መንገድ ባለስልጣን የሚተዳደሩ ናቸው።

በዘርፉ እጅግ አበረታች ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። በሰሜን ጎንደር ዞን የበየዳ፣ የፀለምትና የምዕራብ አርማጭሆ፣ በሰሜን ወሎ ዞን የጨት (ዳውንት)፣ በደቡብ ወሎ ዞን የአርጎባ (የመዲና) እና የበለጨማ (ሳይንት)፣ በሰሜን ሸዋ ዞን የሞላሌ (ወገሬ) ወረዳዎች የመንገድ ግንባታዎች በቅርቡ ሲጠናቀቁ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች በጋ ከክረምት የሚያገናኝ መንገድ ይኖራቸዋል።

ክልሉ ካሉት 3,428 ቀበሌዎች መካከል በአሁኑ ወቅት ሩብ ያህሉ ክረምት ከበጋ የሚያገናኝ መንገድ አላቸው።

የበጋ መንገድ ብቻ ያላቸውንና ምንም መንገድ የሌላቸውን ቀበሌዎች በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ በጋ ከክረምት የሚያገናኙ መንገዶች እንዲኖሯቸው ለማድረግ የተጠናከረ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ነው።







ቴሌኮሙኒኬሽን

ክልሉ ሲመሰረት በተወሰኑ ከተሞች ላይ ብቻ አተኩሮ የነበረው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በአሁኑ ወቅት ዓይነቱና አድማሱ ሰፍቷል፡፡ ከዘርፈ ብዙው የቴሌኮም አገልግሎት ጥቂቶቹን ብቻ ለምሳሌነት ብንጠቅስ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ውስጥ 2,089 ቀበሌዎች የስልክ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ የመደበኛ የስልክ ብዛት 125,219 ደርሷል፡፡

ከ197 ሺህ በላይ ሞባይል ስልኮች ሲኖሩ፣ ይህም በወኪሎች የተሸጡትን ቁጥር አይጨምርም፡፡ የሞባይል ትራፊክ 460,000 የደረሰ ሲሆን 2.4 ሚሊዮን ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችል የሞባይል ኔትዎርክ ተዘርግቷል፡፡ ከመደበኛ ስልኮች በተጨማሪ የኢንተርኔትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች በፍጥነት ተስፋፍተዋል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል

በክልሉ እስከ 1987 ዓ.ም በነበረው ጊዜ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ያገኙ የነበሩት ከተሞችና የገጠር መንደሮች ብዛት 90 ብቻ የነበረ ሲሆን በ2000 ዓ.ም ይህ የከተሞችና የገጠር መንደሮች ብዛት 690 ደርሷል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ያገኙት ከተሞችና የገጠር መንደሮች አጠቃላይ ብዛት 3,400 ያክል ሲሆን፣ የአማራ ክልል ከተሞችና ገጠሮችም ከዚህ ቁጥር 20 በመቶውን ይይዛሉ፡፡

በአገራችን በስፋት እየካተሄደ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንቅስቃሴ እየተጠናከረ በሄደ ቁጥርም በክልላችን አገልግሎቱ ይበልጥ እየጨመረ እንደሚሄድ ይታመናል፡፡

የከተማ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት

በአማራ ክልል በሁሉም ዞኖች ከተሞችን ለሥራና ለኑሮ የተመቹ ለማድረግ ሰፋፊ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ናቸው፡፡ የከተማ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የቆሻሻ መፋሰሻ መስመሮች እንዲሁም ለነዋሪዎች በተመጣጠኝ ዋጋ የሚተላለፉ የመኖሪያ ቤቶችን የመገንባት እንቅስቃሴዎች በስፋት እየተካሄዱ ነው፡፡

እነዚህ የከተማ ልማት እንቅስቃሴችም ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡ ባለፉት ሁለትና ሦስት አመታት ብቻ በተለያዩ ከተሞች እየተገነቡ ከሚገኙት 20,113 የመኖሪያ ቤቶች መካከል 5,460 ያህሉ ለነዋሪዎች ተላልፈዋል፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ዘርፍም የሚታየው እንቅስቃሴ አበረታች ነው፡፡ ወጣቶችና ሴቶች በኮንስትራክሽን፣ በብረትና በእንጨት ፣በምግብ ዝግጅት፣ በከተማ ጽዳትና በሌሎችም የሥራ መስኮች ዙሪያ እየተደራጁ፣ የስልጠናና የብድር አቅርቦት እያገኙ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡

በ1986 ዓ.ም የእነዚህ መስኮች ተጠቃሚዎች ብዛት 7,000 ብቻ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ከ161 ሺህ በላይ አድጓል፡፡

የአማራ ክልል ሕዝብ የልማት ችግሮች በራሱ ወሳኝ ጥረትና በአጋሮቹ ልማታዊ ትብብር ይፈታሉ!

ቱሪዝም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ተልዕኮ የክልሉ ሕዝብ አኩሪ የባህልና የተፈጥሮ እሴቶች እንዲጠበቁና እንዲለሙ በማድረግ ዘላቂ የባህል፣ ቱሪዝምና የጥበቅ ሥፍራዎች ሥርዓት በመዘርጋት ለክልሉና ለሃገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት የላቀ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማስቻል ነው፡፡

በመሆኑም ቢሮው ለአለፉት 17 ዓመታት የክልሉን የተፈጥሮ፣ የባህልና የታሪክ ብዝሃ ሃብቶች፣ እሴቶችና መስህቦች የክልሉን ሕዝቦች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ የማልማት ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል፤ በማከናወን ላይም ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው በዓለም ቅርስነት ሃገራችን ካስመዘገበቻቸው ስምንት ቅርሶች መካከል ሦስቱ በክልላችን ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በቱሪዝሙ ዘርፍ እነዚህንና ሌሎች የክልላችንን መስህቦች በማስተዋወቅ ክልሉ ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ ሆና ቱሪዝም በክልሉ የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ሁለገብ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱት የልማት ዘርፎች አንዱ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡ ቱሪዝሙን ለማልማት መከናወን ካለባቸው ጉዳዮች ውስጥ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ማሟላት ቅድሚያ የሚሰጠው መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም በክልሉ ዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች ለምሳሌ በጉንደር፣ ባህር ዳርና ላሊበላ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ተሰርተዋል፡፡ ራቅ ባሉ መዳረሻዎች ሳይቀር ውሃ መብራትና አዳዲስ የመኪና መንገዶችም ተገንብተዋል፡፡ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትም እንደዚሁ እየተስፋፉ ነው፡፡ ቱሪስቱ በቂ መረጃ እንዲያገኝ የሚያስችሉ /አራት/ የመረጃ ማዕከላት ተገንብተው ከአስር ያላነሱ ካውንስሎች ተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡

በሆቴሉ ዘርፍ ለቱሪስቱ ቆይታ መሠረታዊና አስፈላጊ የሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ቁጥር አድጓል፡፡ ከ1985 ዓ.ም በፊት አምስት የመንግሥት ሆቴሎች

አልማ 1984-2002

ብቻ የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማጐልበት የተወሰዱት የኢኮኖሚ ፖሊሲ እርምጃዎች አበረታች በመሆናቸው 12 ሆቴሎችና ሦስት ሎጁዎች በግል ባለሃብቶች ሊገነቡ ችለዋል፡፡ ከ260 በላይ የአካባቢ አስጐብኚዎች የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን የአስጐብኚ ድርጅቶች ቁጥርም ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡

የክልላችንን የቱሪዝም ሃብት በዘላቂነት ለማልማት ከቱሪዝም ልማቱ የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ቱሪስቱ ተፈጥሮንና ተንዳኝ ባህላዊ እሴቶችን በማየት የሚደሰትበትና የሚደነቅበት፣ ኅብረተሰቡም ንቁ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በማድረግ ተጠቃሚ የሚሆንባቸው ማኅበረሰብ አቀፍ የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴዎች በክልሉ ተስፋፍተዋል፡፡ አውራ አምባ፣ መቄት፣ መቅደላ፣ የሰሜን ተራሮች ፓርክ የመሳሰሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ በቱሪዝሙ ዘርፍ በክልሉ አዳዲስ መዳረሻዎች እየተስፋፉ መምጣት፣ ቱሪስት መጥን የሆኑ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋማት በጥራትና በብዛት በየመዳረሻዎቹ መስፋፋት፣ የፕሮሞሽን ሥራ መሰራትና ህብረተሰቡ ስለጐብኚት ያለው ግንዛቤ እየጨመረ መምጣት፣ ሰላምና መረጋጋት መስፈን የክልላችን የቱሪስት ፍሰቱንና ከቱሪስት የሚገኘውን ገቢ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያድግ አድርጐታል፡፡ ለምሳሌ በ2001 ዓ.ም 71,779 የውጭና 126,261 የሃገር ውስጥ ጐብኚዎች ክልላችንን ጐብኝተዋል፡፡ ከዚህም ከ179 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህ ውጤት ከ1998 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር ከቱሪስት ቁጥር አንፃር በ102%፣ በገቢ ረገድ ደግሞ ከአራት እጥፍ በላይ /425%/ መጨመሩን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በቅርስ እንክብካቤ፣ ጥገናና አሰሳም አበረታች ሥራዎች ተከናውነዋል። በመንግሥት በጀት፣ በውጭ እርዳታና በማኅበረሰብ ተሳትፎ 13 ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናትና አብያተ መንግሥታት ጥገና ሊደረግላቸው ችሏል። እነዚህን ቅርሶች ከዝናብና ከተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ለመታደግም ዘጠኝ የእንጨትና አንድ የብረት መጠለያዎች ተሰርቶላቸዋል። የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንዲቻልም 666 ቋሚና 20,500 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ሊመዘገቡ ችለዋል።

በፓርኮች ዘርፍ በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና ህይወታዊ ሃብቶችና የተፈጥሮ ቅርሶችን በፓርክነት ወይም መሰል ጥብቅ ሥፍራነት ተለይተው በተሻለ ሁኔታ ለምተውና ተጠብቀው ለመጭው ትውልድ እንዲተላለፉ የሚያስችል ሥራ ለመስራት የተደረገው ጥረትና እንቅስቃሴም ውጤታማ ነበር። 266,570 ሄክታር ስፋት ያለው የአላጥሽ እንዲሁም 4,375 ሄክታር ስፋት ያለው የቦረና ሳይንት ብሔራዊ ፓርኮች ሆነው እንዲቋቋሙ ተደርጓል። ከእነዚህ ፓርኮች ሌላ የአባይ ሸለቆን እንዲሁም በአዊ ዞን በጃዊ ወረዳ ውባጉማዋ በሚል የሚታወቀውን የተፈጥሮ ደን የብዝሃ ሕይወት ሃብት በጥብቅ ሥፍራነት ለመከለል የሚያስችል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

የስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ የተጋረጡበትን ሥጋቶች በማስወገድ በዘላቂና አስተማማኝ ደረጃ በማልማትና በመጠበቅ ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለአካባቢው ኅብረሰተብ የኑሮ መሻሻልና ለክልሉ አጠቃላይ ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከእነዚህም ውስጥ በፓርኩ ውስጥና በዙሪያው ሰፍረው የሚገኙ ነዋሪዎች እያደረሱ ያለውን አሉታዊ ሁኔታ ለመቀነስ የዱር እንስሳ መተላለፊያ በሆኑት አካባቢዎች ለሰፈሩ 144 አባወራዎች ተተኪ ቦታ በማዘጋጀትና ካሣ በመክፈል ከፓርኩ ክልል ውጭ እንዲሰፍሩ ተደርጓል። ለአካባቢው ኅብረተሰብም ከ1,000 በላይ የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ተሰራጭቷል። የዋልያና የቀይ ቀበሮ ዋነኛ መናኸሪያ በሆኑ አካባቢዎች የቤት እንስሳት እንዳይሰማሩ ተጨማሪ 30 ሄክታር

የባቲ መስጊድ

የባቲ ልጃገረዶች





ቦታ በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲከበር ተደርጓል። በመሆኑም በ1997 ዓ.ም በቆጠራ የተገኙት 567 ዋልያዎች እንዲሁም ቀይ ቀበሮ 712 የነበሩ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ዋልያ በ28፣ ቀይ ቀበሮ በ84 ጭማሪ ሊታይባቸው ችሏል።

በባህሉ ዘርፍ ቢሮው ለስነ ጥበብና ባህል መዳበርና መስፋፋት ልዩ ትኩረት በመስጠት 478 ክበባት ስልጠና ተሰጥቷቸው ሊደራጁ የቻሉ ሲሆን፤ በየሁለት ዓመቱ ክልል አቀፍ የሥነ ጥበባት ውድድሮችን በየዓመቱ ደግሞ እንዲሁ ክልል አቀፍ የኪነ ጥበባት ውድድሮች ይካሄዳሉ። እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ ሰባት ፌስቲቫሎችና 12 ውድድሮች ተካሂደዋል።

በፌስቲቫልም ሆነ በውድድር አሸናፊ ለሆኑ ተወዳዳሪዎች የማትጊያ ሽልማቶች ከመስ ጠታቸውም ባሻገር ሥራዎቻቸው ስፊ መድረክ እንዲያገኙና ለትውልድ እንዲተላለፉ በመጽሐፍ እንዲታተሙላቸው ተደርጓል። በዚህ መልኩ በየሁለት ዓመቱ "መቅረዝ" በሚል ርዕስ እየተዘጋጁ አምስት መጽሐፍት በ15,000 ኮፒ ታትመው ለኅብረተሰቡ በነፃ ተሰ ራጭተዋል።

የባህል ሥራዎች የሚከወኑባቸውና ለሕዝብ የሚቀርቡባቸው መረጃዎች የሚጠበቁባቸውና ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸው የባህል ተቋማትን በመገንባትና በማስፋፋት ረገድም የሚያበረታታ ተግባር ተከናውኗል። አንድ ሁለገብ አገልግሎት የሚሰጥ /ሙሉ ዓለም/ የባህል ማዕከልና 13 የሕዝብ ቤተመፃሕፍት ከአልማ ጋር በመተባበር የተገነቡ ሲሆን፤ ሌሎች የውስጥ አደረጃጀታቸውን በማሻሻልና በማስፋፋት አገልግሎት እንዲሰ ጡ የተደረጉ 48 ቤተመፃሕፍትና 5 ሲኒማ ቤቶች፣ እንዲሁም 119 ንባብ ቤቶች ይገኛሉ።

የሻደይ ጨዋታ በዋግ ኽምራ

ሰሠ 1984-2002





የክልሉ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት መገለጫ የሆኑ በርካታ የባህል፣ የታሪክና የቋንቋ ጥናቶች ተካሂደዋል። በክልሉ ውስጥ ከዘመኑ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ጋር የማይጓዙና የዕድገት ማነቆ የሆኑ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች የተስፋፉበት እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይሁንና ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላትና ከኅብረተሰቡ ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በመፍጠር ህብረተሰቡን በማወያየትና በማሳመን እነዚህን ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች ለመከላከልና ለማስወገድ ያላሰለሰ ጥረት በመደረጉ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ እንደቀነሱ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

ክልላዊ የውሃ ሃብት አቅም

የአማራ ብሄራዊ ክልል 170,150 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው፡፡ ክልሉ ሰፊ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ባለቤት ነው፡፡ ለአብነት ለመጥቀስ ያክል 6,900 ካሬ ኪ/ሜትር ከሚሸፍኑት የአገራችን 15 ዋና ዋና ሀይቆች መካከል 3,600 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውና ከሃገሪቱ ቀዳሚ የሆነው የጣና ሃይቅ በክልሉ ይገኛል፡፡ ከዚህ ሌላ የ14 አነስተኛ ሃይቆች፣ ኩሬዎችና ፍል ውሃዎች ባለቤት ነው፡፡ በተጨማሪም አገሪቱ ካሏት ዋና ዋና የወንዝ ተፋሰሶች መካከል አራቱ በክልሉ የሚገኙ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የአባይ ተፋሰስ 45 በመቶ፣ የተከዜ ተፋሰስ 30 በመቶ፣ የአዋሽ ተፋሰስ ደግሞ 18 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናሉ፡፡ በአጠቃላይ በሦስቱ ተፋሰሶች የሚገኙ ወንዞች አማካኝ የፍሰት መጠናቸው 35 ቢሊየን ሜትር ኪዩብ ውሃ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከዚህ ሌላ አመቱን ሙሉ የሚፈሱ 497 አነስተኛና መካከለኛ ወንዞች 297 ጨረታዎች /ወቅታዊ ወንዞች/፣ 2,860 ምንጮችና ሰፊ የሆነ የከርሰ ምድር ውሃ ባለቤት ሲሆን፣ መታደስ ከሚችለው የአገራችን የገፀ ምድር ውሃ ውስጥ ከ21-29 በመቶ የሚሆነው በክልሉ ይገኛል፡፡

ይህን ሰፊ ሀብት ማልማት፣ ማስተዳደር፣ መጠበቅ እና የላቀ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው ለማስቻል የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የክልሉን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ሲያደራጅ ውሃ ሃብት ልማት ቢሮን አቋቁሟል፡፡

ቢሮው በዚህ መልክ ከተቋቋመ በኋላ የኤ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የተቀናጀ የውሃ ሃብት አስተዳደር ፖሊሲን እና የተቋሙን ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት አድርጎ በውስጡ ሁለት አላማ ፈጻሚ ዘርፎችን ማለትም:- የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍና የመስኖ ተፋሰስ ልማት ዘርፍን አደራጅቷል፡፡ ከዚህ በማስከተልም፣ ሦስተኛውን ስትራቴጅክ እቅድ (ከ1998 -2002 ዓ.ም) አዘጋጅቷል፡፡ ምንም እንኳ የስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ ሠኔ 30/2002 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ቢሆንም፤ ያለፉት አራት ዓመታት አፈፃፀማችን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የአምስት አመት መርሃ ግብራችን መነሻ ሁኔታዎች

ከ1998 -2002 ዓ.ም ድረስ የሚቆየው ሦስተኛው ስትራቴጅክ እቅድ የተዘጋጀው ሁለት መሠረታዊ መርሃ ግብሮችን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሁሉን አቀፍ የንጹህ መጠጥ ዉሃ ተዳረስ መርሀ ግብር /UAP/ ፕሮግራሙ ከምዕተ

ዓመቱ የልማት ግብ ሁለት አመት ቀደም ብሎ የሚፈጸም ነው፡፡

በዚህ ፕሮግራም መሠረትም፣ በገጠር ለሚኖሩ ህዝቦች ከሚኖሩበት አካባቢ 1.5 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ በቀን በአማካይ ለአንድ ሠው 15 ሊትር ንፅህናው የተረጋገጠ ውሃ ለማቅረብ፣ እንዲሁም ለከተማ ነዋሪው ከሚኖርበት አካባቢ በ500 ሜትር ርቀት በቀን በአማካይ ለአንድ ዜጋ 20 ሊትር ውሃ ለማቅረብ የተያዘው መርሃ ግብር ታሣቢ ተድርጓል፡፡

ሁለተኛው የፈጣንና ዘላቂ ልማት እና ድህነት ቅነሣ አገራዊ እቅድ (PASDEP) በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፀው ከ1998 -2002 ሲሆን፣ በዚህ መርሃ ግብር ትኩረት ከተሠጣቸው የመስኖ ልማትና የንፁህ መጠጥ ውሃ ማዳረስ ተግባራት ጋር የተያዙ ግቦችንም መሠረት አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት፣ የአብክመ ውሃ ሃብት ልማት ቢሮ በንፁህ መጠጥ ውሃ ዘርፍና በመስኖ ተፋሠስ ልማት ዘርፍ በ1998 -2002 ዓ.ም መሪ እቅድ የሚከናወኑ ተግባራትን አስፍሯል፡፡

ምን አቅደን ምን ሰራን?

1. የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ዕቅድ - የአራት ዓመት ክንውን

ተ.ቁ	የውሃ ተቋሙ ዓይነት	ለ1998-2002 የታቀደ	እስከ ሰኔ 30/2001 ዓ.ም		አፈፃፀም በመቶኛ
			የታቀደ	የተፈፀመ	
1	የእጅ ጉድጓድ	10,735	8,665	7,428	
2	ምንጭ ማጐልበት	8,347	6,625	4,587	
3	መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ	1,248	1,025	680	
4	ጥልቅ ጉድጓድ	185	135	90	
	ድምር	20,515	16,450	12,785	77.7

ሠንጠረዥ-1. የገጠር ንጹህ መጠጥ ዉሃ ግንባታ የአራት አመት አፈጻጸም

ተ.ቁ	ተግባራት	ለ1998-2002 የታቀደ	እስከ ሰኔ 30/2001 ዓ.ም የታቀደ	እስከ ሰኔ 30/2001 ዓ.ም የተፈፀመ	አፈፃፀም በመቶኛ
1	የጥናትና ዲዛይን ስራ	110	81	72	
2	አዳዲስ ግንባታ	126	54	54	
3	የማስፋፊያና ማሻሻያ ስራ	46	35	40	
	ድምር	282	170	166	

ሠንጠረዥ-2. የከተማ ንጹህ መጠጥ ዉሃ የአራት አመት አፈጻጸም

በንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት የ18 ዓመት ጉዞ

ስለአማራ ክልል ንፁህ የመጠጥ ውሃ ሽፋን በ1983 ዓ.ም የተመዘገቡና የተቀመጡ ሰነዶችን ብናይ፣ በወቅቱ በጠቅላላው በክልሉ በገጠር 1,780፣ በከተማ 262 የውሃ ተቋሞች ብቻ እንደነበሩ እንገነዘባለን:: እነዚህ ተቋማትም በገጠር ይኖር ከነበረውና ከ12 ሚለየን በላይ ከሚገመተው ህዝብ መካከል ለ5 በመቶ ወይም 660 ሺህ ለሚሆነው ሕዝብ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ነበሩ::

በአንጻራዊነት ሲታይ የከተማው ሽፋን ከገጠሩ የተሻለ ቢመስልም፣ ዝቅተኛ መሆኑ ግን ብዙ አያነጋግርም:: ይኸውም በወቅቱ በክልሉ ከተሞች ይኖር ከነበረው ሕዝብ ውስጥ 750 ሺህ የሚጠጋው ወይም 30 በመቶው ብቻ የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆን፣ ቀሪው ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ አልነበረም:: በአጠቃላይ ከዚህ መረጃ የምንገነዘበው ቅድመ 1983 ዓ.ም. የገጠርና ከተማ አጠቃላይ የንፁህ መጠጥ ውሃ ክልላዊ ሽፋን 10 በመቶ ብቻ እንደነበር ነው:: በመቀጠል፣ ቢሮው 1997 ዓ.ም. የመጀመሪያውን ስትራቴጅክ እቅድ ሲያጠናቅቅ ሽፋኑ በገጠርና ከተማ ከ5 በመቶ ወደ 31 በመቶ ከፍ ሲል፣ በከተማ ደግሞ ከ31 በመቶ ወደ 78 በመቶ አድጓል:: የሁለተኛው ስትራቴጅክ እቅድ ዘመን/1998 - 2002 ዓ.ም ባይጠናቀቅም፣ ባሣለፍናቸው ሦስት ዓመታት በተደረጉ ጥረቶች የገጠሩን ሽፋን ወደ 49 በመቶ፣ የከተማውን ደግሞ ወደ 84.5 በመቶ በማሣደግ ግስጋሴውን ቀጥሏል::

መግለጫ	መለኪያ	ከ1983 ዓ.ም. በፊት	1993 - 1997 ዓ.ም. የተደረሰበት	1998-2002 ሰኔ/30 2001 የተደረሰበት
የገጠር መጠጥ ውሃ				
- የውሃ ተቋማት ብዛት	በተቋም	1¸780	10¸205	22¸990
- ተጠቃሚ ህዝብ	በቁጥር	659¸635	5¸245¸858	8¸530¸348
- ሽፋን	በመቶኛ	5%	31%	54%
የከተማ ን/ መጠጥ ውሃ				
- የውሃ ተቋማት	በተቋም	262	366	435
- ተጠቃሚ ህዝብ	በቁጥር	746¸632	1¸672¸563	2¸084¸433
- ሽፋን	በመቶኛ	30%	78%	87%
ክልላዊ ማጠቃለያ				
- የውሃ ተቋም	በተቋም	2¸042	10¸571	23¸425
- ተጠቃሚ ህዝብ	በቁጥር	1¸406¸284	6¸918¸421	10¸614¸781
- ሽፋን	በመቶኛ	10%	36%	58%

ሠንጠረዥ- 3. የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ወቅታዊ ሁኔታ

2/ የመስኖ ተፋሰስ ልማት ዘርፍ ዕቅድና ክንውን

በክልሉ በእርጥበት አጠር አካባቢዎች 12,650 ሄክታር፣ በቂ እርጥበት ባላቸው ደግሞ 5,650 ሄክታር፣ በድምሩ 18,300 ሄክታር ሊሸፍን የሚችል የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ስራ ይከናወናል:: በተጨማሪ፣ በቂ እርጥበት ባላቸው 2፣ በቂ እርጥበት በሌላቸው 3 ፣በአጠቃላይ 5 የመስኖ ልማት ማስተር ኘላን በንዑስ ተፋሰስ ደረጃ ይዘጋጃል::

በግንባታ ዙሪያ:- 16,513 ሄክታር የሚሸፍን የአነስተኛ ዘመናዊ መስኖ ልማት ኘሮጀክቶች ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን፣ 20,700 ሄክታር መሬት የሚሸፍን የአነስተኛ ዘመናዊ መስኖ ልማት ኘሮጀክቶች የጥገና ስራ ይሰራል::

በአጭሩ፣ እቅዱ ይህን ይመስል ነበር::

የመስኖ ተፋሰስ ልማት ዘርፍ የ18 ዓመት ጉዞ ሲዳሰስ

በዚህ ዘርፍ የተገኘው መረጃ እንደሚያሣየው፣ በ1988 ዓ.ም 2,658 ሔክታር መሬት በማልማት 10,632 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 12 ዘመናዊ የመስኖ ግንባታዎች ነበሩ:: ከ1989 — 1996 ዓ.ም ባለው ጊዜ ዘርፉን ለማልማት በተደረገው ጥረት 6,343 ሄክታር መሬት ማልማትና 27,219 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 114 የመስኖ ተቋሞች ተገንብተዋል:: ከ1997 — 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ደግሞ 19,466 ሄክታር መሬት በማልማት 45,889 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 165 የመስኖ ግንባታዎች ተከናውነዋል::

በአጠቃላይ፣ በክልላችን ዘመናዊ የመስኖ ግንባታዎችን ማከናወን ከጀመርን አንደኛውን አስርተ ዓመት አጠናቀን ሁለተኛውን እየጀመርን ቢሆንም፣ በዘርፉ ተጠቃሚነታችንን ለማሣደግ በተደረገው ጥረት 28,467 ሄክታር አልምተው 83,740 አርሶአደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 291 ዘመናዊ፤ አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ አውታሮች ተገንብተዋል::

ተ.ቁ	የተገነቡበት ዘመን	ብዛት (በተቋም)	የለማ መሬት (በሔክታር)	የተጠቃሚ ብዛት
1	ከ1983 በፊት	-	-	-
2	1984 -1988	12	2,658	10,632
3	1989- 1996	114	6,342.6	27,219
4	1997- 2000	165	19,466.2	45,889
	ጠቅላላ ድምር	291	28,465.8	83,740

ሠንጠረዥ-6. የመስኖ ግንባታ እድገት ብዛት፣ የለማ መሬትና ተጠቃሚ

የመስኖው ዘርፍ የልማት ውጥኖቻችን

ከዚህ በተጨማሪ፣ ያለንን የውሃ ሃብትና በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ጥቅም ላይ ለማዋል በፌዴራል መንግስት የታቀዱና በግንባታ ሂደት ያሉ ዘጠኝ ከፍተኛ ግድቦች ሲኖሩ፣ እነዚህም መንግስት ዘርፉን ለማልማት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ፣ ከፍተኛ ግድቦች ሲጠናቀቁ 128,551 ሄክታር መሬት በማልማት ሚሊዮኖችን ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

በክልላችን በግንባታ ሂደት ያሉ ከፍተኛ ግድቦች

ተ.ቁ	የግድቡ ስም	የግድቡ ዓይነት	ከፍታ በሜትር	ውሃ የመያዝ አቅም በሜ^3	የውሃ ስፋት በሔክታር	የሚያለሙት መሬት በሄክታር	ስራው ያለበት ደረጃ
1	ቆጋ	የአፈር ግድብ	8	--	600	7000	አብዛኛው የተጠናቀቀ
2	መገጭ	ኮንክሪት ግድብ	80	270	1160	7311	በግንባታ ላይ ያለ
3	ርብ	ኮንክሪትና አፈር ግድብ	58	194	895	19925	በግንባታ ላይ ያለ
4	ጀማ	>>	70	173	737	7786	በግንባታ ላይ ያለ
5	ግልገል አባይ1	ኮንክሪት ግድብ	39	115	937	12069	በዝግጅት ላይ ያለ ጥናቱ ተጠናቆ
6	ግልገል አባይ2	>>	60	563	2452	11508	>>
7	ጉማራ 1	የድንጋይ ግድብ	65	355	1200	13979	>>
8	ጉማራ 2	>>	70	340	1090	13976	>>
9	ጣና በለስ	>>	-	-	-	35,000	>>
	ጠ/ድምር			2010	9071	128,551	

ሠንጠረዥ - 8. በግንባታ ሂደት ያሉ ከፍተኛ ግድቦች



አማራ አቀፍ ልማት ማህበር
ዋና ጽ/ቤት
AMHARA
AMHARA DEVELOPMENT ASSOCIATION A.D.A
አማራ አቀፍ ልማት ማህበር
/አልማ/